

# አንዳንዴ ሀገሬን ሳስባት...

ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ

**አንዳንዴ ሀገሬን ሳስባት፣
ፋብሪካ ትመስለኛለች፣ ኢህአዴግ የገነባት፤
ዜጎቿን ጥሬ እቃ አድርጎ፣
ዜጎቹን የሚያመርትባት።**

የአንድ ሀገር ዜጋ ሁሉ እንዴት አንድ አይነት ሃሳብ፣ ተመሳሳይ እውነትና እውቀት ሊኖረው ይችላል? እንዲህ አይነቱስ ፍላጎት ከወዴት ይመነጫል? መቼስ ሰው የሽራ ጫማ ወይም የኮካ ጠርሙስ ይመስል ተመሳሳይ ሊሆን አይችልም። ሰው አፈጣጠሩ ከአንድ ፋብሪካ ቢሆን እንኳ ቤተሰቡ፣ ቀዬው፣ ባህሉ ለየቅል ያበጁትና የኋላ ኋላ እራሱን ይሆናል- የተለየነቱን። ይህ እጅግ ግልጽ እውነትና ቀላል እውቀት ነው። ይሁን እንጂ በተለያዩ ሀገሮች በየዘመናቱ የተነሱና የነገሱ፣ የተመረጡና የተመረጠውን የፈነቀሉ መንግስታት፤ ለዚህ ጸሐይ የሞቀው እውነት ደንቁረው በነገሱበት ሀገር ያለውን ዜጋ ሁሉ፣ በአንድ አይነት ፖለቲካዊ አስተሳሰብና ማህበራዊ አመለካከት ሊገሩት ሲውተረተሩ መንግስታዊ እህል ውሀቸው አልቋል።

የእነዚህ አይነቶቹ መንግስታት ዋናው መገለጫ የሃሳብና የአመለካከት ልዩነትን አለመፍቀዳቸው ነው። እንኳን በዜጎች መካከል፣ በራሳቸው መንግስቱን በገነቡት አባላት/ባለስልጣናት መካከል የሃሳብ ልዩነትን አይፈቅዱም። እነሱ የሚከተሉት ጽንሰ-ሃሳብና ትወራ ቅዱስ ነውና ከዚያ የተዛረረ ደግሞ እርኩስ ይሆናል። ለዚህም ግባቸው መንግስታቱ የማያረክሱት ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ማህበራዊ እሴት የለም። ይህ አይነቱ አስተሳሰብ በተለይ በሶሻሊስት ሀገሮች መንግስታት ተግባራዊ ሲደረግ እንደነበረ የአለማችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። ከሶሻሊዝም መውደቅ በኋላ ግን ይህን አይነቱ መንግስታዊ አስተሳሰብ፤ በተለይ በስልጡኑት ምእራባዊ ሀገራት አፀያፊና አሳፋሪ ሆኗል። ይሁን እንጂ በአፍሪካና በሌሎች ያላደጉ ሀገሮች አሁንም የበርካታ መንግስታት መገለጫ እንደሆነ ነው።

አሁን አሁን፣ በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ ደግሞ የሀገሬን ሁኔታ ስመለከት፤ ኢህአዴግን ከነዚህ አይነቶቹ መንግስታት እመድበዋለሁ። ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ከ1983 ዓ.ም ጀምሮ በፖለቲካዊና ማህበራዊ አስተሳሰቡ ላይ መሰረታዊ ለውጥ አላደረገም። ከሀገር ውስጥና ከውጭ ምሁራን የቀረቡ የጥናት ውጤቶች፣ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች የተሰነዘሩ አቅጣጫዎች፣ ከህዝብ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በኢህአዴግ አመለካከት ላይ ቅንጣት ለውጥ አላመጡም። በብሔራዊ ማንነት ላይ የተመሰረተ፣ ብሔር-ብሔረሰባዊና ግለሰባዊ ማንነት ከመገንባት ይልቅ፣ በብሔር-ብሔረሰባዊ /ጎሳዊ/ ማንነት ላይ የተገነባ ግላዊ ማንነትን የሚያራምድና ብሔራዊ ማንነትን ከቁብ ያላስገባ፣ ፖለቲካዊ አስተሳሰቡን ለረባ ህዝባዊ ውይይት (ዲያሎግ) ለማቅረብ እንኳ የነበር አራስ እንደሆነ አለ።

በመሆኑም የሀገሬ ዜጎች በሙሉ በጎሳዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ አምነው እንዲጠመቁ፣ ለሚደረገው ቁሳዊ ልማት እንዲዘምሩ ይጠበቃል። ይህን ፖለቲካዊ አስተሳሰብና ቁሳዊ ልማት የማይቀበሉ ወይም የተለየ ሃሳብ ያላቸው በኢህአዴግ ዘንድ ለሀገራቸውና ለወገናቸው የማያስቡ (አሸባሪ፣ ጨለምተኛ፣ ኪራይ ሰብሳቢ፣ ፀረ ልማት...) ተደርገው ይቆጠራሉ።

እዚህ ላይ መንግስት የተለየ አስተሳብ ያላቸውን ሰዎች የተለያየ ስም በመስጠት ብቻ ቢያቆም ባልከፋ፣ በጉልበትም ሆነ በፕሮፖጋንዳ የራሱን አመለካከት የተቀበሉ ዜጎች አድርጎ እንደገና ሊፈጥራቸው ወሰን-አልባ ተግባር ያከናውናል። ከደቡብ እስከ ሰሜን፣ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ያሉ ዜጎች ሁሉ ከዚህ ተጽዕኖ አያመልጡም። ኢህአዴግ በሳምንት ሰባት ቀን፣ በቀን ሃያ አራት ሰዓት በፕሮፖጋንዳ እያቀለጡ የሚቀጠቅጡ፣ ቀጥቅጠው የሚያጎብጡ የብዙሃን መገናኛዎች አሉት። የመገናኛ ብዙሃን፤ የሀገሬ ዜጎች አመለካከት ተጨፈላልቆ፣ አንድ ወጥ አስተሳሰብ እንዲይዙ የሚደረጉበት ፋብሪካና የመቆጣጠሪያ ነጥቦች ናቸው። አንዳንዴ ጉልበታቸው ሲደክም፣ አቅማቸው ሲያጠራጥር ደግሞ አዋጆችና መግለጫዎች ያግዟቸዋል።

የመገናኛ ብዙሃን ያላቸው የመለወጥ ሀይል ከጦር ሃይል የላቀ ስለመሆኑ አሌ የማይባል ቢሆንም፣ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ የግል ራዲዮና ቴሌቪዥን በሌለበት ሀገር ማናቸው እጅግ የጎላና ፈጣን ነው። (በነገራችን ላይ በሀገራችን ያሉት አንድና ሁለት የግል ኤፍ ኤም ራዲዮ ጣቢያዎች እንኳ መንግስት በፈቀዳቸው ጉዳዮች ላይ ብቻ የሚያተኩሩ እንጂ መንግስትን ሞግተው ለውጥ የሚያመጡና የፋብሪካውን አሰራር የማስተካከል አቅም ያላቸው አይደሉም።) የመገናኛ ብዙሃን ስለተዘረጋልን ጎዳና፣ ስለተገነባው ህንፃና ፋብሪካ... በአጠቃላይ ስለቁሳዊው ልማት ሃያ ሰአት ያወራሉ። የተረፈውን አራት ሰዓት ደግሞ መንግስት ቁልቁል እንዲያድግ የፈቀደውን የዜጎችን ህሊናዊ ልማት ለማቆርቆዝ ይጠቀሙበታል። የዜጎች ባህላዊ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ማንነት መልማት እንዳለበት አውቀው፣ በሃላፊነት የሚሰሩ የራዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች በሃገራችን የሉም ለማለት ይቻላል። እዚህ ላይ አንዳንድ የዜጎችን ህሊናዊ ልማት ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ነጠላ ፕሮግራሞች ያላቸው (እንደ ሸገር ኤፍ. ኤም ያሉ) ጣቢያዎች መኖራቸው የሚታይ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህም ጣቢያዎች ቢሆኑ በዜጎች ማንነትና በሀገራዊ እሴቶች ላይ የሚሳለቁ ፕሮግራሞች (የሰይፉ ፋንታሁንን ታዲያስ አዲስ ልብ ይሏል) የሚተላለፉባቸው በመሆኑ፣ በነዚህ ጣቢያዎች አማካይነት የሚተላለፉት ፕሮግራሞች፤ በፖሊሲ ተነድፈውና በቅድሚያ ታቅደው የሚዘጋጁ ሳይሆን፣ ቢዝነስ (ገንዘብ) የሚያሽከረክራቸው የመንግስታዊው የአስተሳሰብ መጨፍለቂያ ጣቢያዎች ከመሆን አይዘሉም።

በነገዬቱ ኢትዮጵያ ኢህአዴግ የሚፈልጋቸው ዜጎች፣ በቅድመ-ኢህአዴግ ዘመን በጨቋኝ ብሔር-ብሔረሰቦች የደረሰባቸውን በደል አብዝተው የሚያወሩ፤ የራሳቸውን ብሔር-ብሔረሰብ ገድል አብዝተው የሚጽፉ፤ ከቋንቋቸውና ከባህላቸው በስተቀር የሚገልፃቸው ሰብአዊ አባባ እንደማይገኝ የሚከራከሩ፣ ሃይማኖታዊ እምነታቸውን ሳይቀር ከብሔር-ብሔረሰባዊ ማንነታቸው ጋር አቆራኝተው የሚበይኑ ናቸው። ታዲያ እነዚህን ዜጎች ለማፍራት የመንግስታችን የኢህአዴግ ፋብሪካ በሚገባ እየሰራ መሆኑን ከሚያመለክቱት ጠቋሚዎች ውስጥ ዋንኞቹ የብዙሀን መገናኛዎች ናቸው። . . . አንድ የቅርብ ምሳሌ እነሆ!

የዚህ አመት የትንሳኤ በአልን ምክንያት በማድረግ በኢቲቪ የቀረበውን ልዩ ዝግጅት ተመልክታችኋል? ከየት ነው የተላለፈው? ያልተመለከተ ሰው መቼም የሚገምተው ከቤተ- ክርስቲያን ወይም ደግሞ የበአሉን ምንነት እንዲያንፀባርቅ ተደርጎ ከተዘጋጀ ስፍራ ብሎ ሊመልስ ይችላል፤ አይደለም። ትንሳኤ የተላለፈው የቁሳዊ ልማታችንን መሳለጥ ከሚናገር የብረት ሳጥን ውስጥ ነው፤ በዚህ ቦታ ወይም በዝግጅቱ ላይ የጌታችንን የእየሱስ ክርስቶስ ስቅለትም ሆነ ትንሳኤ የሚያመለክት አንዳችም ነገር (ምስል እንኳን) አልተቀመጠም። እንዲህ አይነቶቹ ድርጊቶች የሚጠቁሙን መንግስት የእኛን የዜጎቹን ሁለንተናዊ ማንነት እየጨፈለቀ የሚያልማቸውን ዜጎች ለማፍራት እንደቆረጠ ብቻ ሳይሆን፣ ጭካኔው እስከምን ድረስ እንደሚሄድ ነው። .....የዚህን ውጤት ደግሞ እየተመለከትን ነው፤ በኢቢኤስ የቴሌቪዥን ፕሮግራም አርቲስት ግሩም ኤርሚያስ በካናቢስ ጀዝቦ ሲናውዝ አድናቆታቸውን የገለጹት የስቱዲዮ ታዳሚዎች፣ ግላዊ ማስተዋላቸው ተጨፍልቆ በአዲሱ የኢህአዴግ ፋብሪካ የተመረቱ የወደፊታችን ማሳያዎች ናቸው። □

**ትንሳኤ የተላለፈው የቁሳዊ ልማታችንን መሳለጥ ከሚናገር የብረት ሳጥን ውስጥ ነው፤ በዚህ ቦታ ወይም በዝግጅቱ ላይ የጌታችንን የእየሱስ ክርስቶስ ስቅለትም ሆነ ትንሳኤ የሚያመለክት አንዳችም ነገር (ምስል እንኳን) አልተቀመጠም። እንዲህ አይነቶቹ ድርጊቶች የሚጠቁሙን መንግስት የእኛን የዜጎቹን ሁለንተናዊ ማንነት እየጨፈለቀ የሚያልማቸውን ዜጎች ለማፍራት እንደቆረጠ ብቻ ሳይሆን፣ ጭካኔው እስከምን ድረስ እንደሚሄድ ነው**